በጀርመን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ኤምባሲ በርሊን
Embassy of the F.D.R
of Ethiopia to F. R. of Germany, Berlin

ቀን
Date 13/06/2016
ቁጥር
Ref. No. በኢ፣ኤ.25/1/906/16

ለሚመለከታቸዉ ክፍሎች ሁሉ

<u>ባሉበት</u>

ጉዳዩ፦ <u>በጀርመን እና ሚሲዮኑ በሚሸፍናቸዉ አገራት ትምህርታቸዉን እየተከታተሉ የሚገኙ ዜጎች ይመለከታል፤</u>

ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የካቲት 12 ቀን 2016 ዓ/ም በቁጥር T.SD/352/16 በተጻፈልን ደብዳቤ መሰረት በተለያዩ የአለማችን አገራት ዩኒቨርስቲዎች የትምህርት ዕድል አግኝተዉ እና ትምህርታቸዉን አጠናቅቀዉ ወደ አገር ቤት ከመመለሳቸዉ በፊት ትምህርታቸዉን በተከታተሉበት አገር በዉጭ ጉደይ ሚኒስቴር ወይንም በሚመለከተዉ የመንግስት ተቋም ትምህርታቸዉን በአግባቡ ስለማጠናቀቃቸዉ የተሰጣቸዉን ማስረጃ ካረጋገጡ በኃላ በዚያ አገር በሚገኘዉ (ሀገሪቱ በሚሸፍነዉ) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ኤምባሲ ወይንም ቆንጽላ ጽ/ቤት ዶክመንታቸዉን ማረጋገጥ እንደሚጠበቅባችሁ እና የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣንም በተለያዩ አገራት ትምህርታቸዉን በተሳካ ሁኔታ አጠናቅቀዉ ለሚመለሱ ተማሪዎች የተሰጣቸዉ ዶክመንት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መረጋገጡን በማየት የአቻ ግመታ እንደሚሰጥ ተገልጾልናል።

በዚሁ መሰረት በጀርመን እና ሚሲዮኑ በሚሸፍናቸዉ አገራት ዩኒቨርስቲዎች የትምህርት ዕድል አግኝታችሁ እና ትምህርታችሁን አጠናቅቃችሁ ወደ አገር ቤት ከመመለሳችሁ በፊት ትምህርታችሁን በተከታተላችሁበት አገር በዉጭ ጉደይ ሚኒስቴር ወይም በሚመለከተዉ የመንግስት ተቋም ትምህርታችሁን በአግባቡ ስለማጠናቀቃችሁ የተሰጣችሁ ማስረጀ እንዲረጋገጥላችሁ ከደረጋችሁ በኃላ በጀርመን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ኤምባሲ የትምህርት ማስረጃችሁን በማረጋገጥ እና ወደ አገር ቤት ከተመለሳችሁ በኃላ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የቆንጽላ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ዶክመንቶቹን በማረጋገጥ በከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን የአቻ ግመታ እንደሚሰጥ በመረዳት በዚሁ ሕደት መሰረት የትምህርት ማስረጃችሁን እንዲረጋገጥላችሁ እንድታደርጉ እያሳሰብን በጀርመን እና ሚሲዮኑ በሚሸፍናቸዉ አገራት የምትገኙ የኢትዮጵያውያን እና ትዉልደ የኢትዮጵያውያን አደረጃጀቶችም ከላይ በተገጸዉ መሰረት ግንዛቤ በመፍጠር አስፈላጊዉ ድጋፍ እንደታደርጉ በአክብሮት እንጠይቃለን።

ከሰላምታ ጋር

Terefe Furgassa Refu
Minister

Boothstrasse 20a
12207 Berlin,
Germany
Telefon: 030-772 06-0/10
Telefax: 030-772 06-26
E-Mail: berlin.embassy@mfa.gov.et
Consulate section: Telefax: 030-772 06 24
E-Mail: info.berlin@mfa.gov.et
www.aethiopien-botschaft.de

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF FORIEGN AFFAIRS

ቀን / Date. የካቲት 1 2 2016

ቁጥር / No. ፓ.ፍ.ኦ/352/16

ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ኤምባሲዎች፣ ቋሚ መልዕክተኛ ጽ/ቤቶች እና ቆንስላ ጽ/ቤቶች

<u>በያሉበት</u>

ኢትዮጵያውያን በተለያዩ የአለማችን አገራት ዩኒቨርስቲዎች የትምህርት እድል አግኝተው ለሚሄዱ ተማሪዎች ትምህርታቸው አጠናቅቀው ወደ አገር ቤት ከመመለሳቸው በፊት ትምህርቱ በተከታተሉበት አገር በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይንም በሚመለከተው የመንግስት ተቋም ትምህርታቸውን በአግባቡ ስለማጠናቀቃቸው የተሰጣቸውን ማስረጃ ካረጋገጡ በኋላ በዚያው አገር በሚገኘው (ሀገሪቱን በሚሸፍነው) ኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ኤምባሲ ወይንም ቆንስላ ጽ/ቤት ዶክመንታቸው ተረጋግጦ ወደ ሀገር ሲገባ፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የቆንስላ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ዶክመንቶቹን መረጋገጥ ይጠበቅበታል። የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣንም በተለያዩ አገራት ትምህርታቸውን በተሳካ ሁኔታ አጠናቅቀው ለሚመለሱ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ዶክመንት በኢ.ፌ.ድ.ሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መረጋገጡን በማየት የአቻ ግመታ ይሰጣል። ይህ ካልሆን ከውጭ አገር የሚገባ የትምህርት ማስረጃ አገር ውስጥ አገልግሎት ላይ የማይውል መሆኑን ባለማወቅ ዜጎች ለእንግልትና ለተጨማሪ ወጪ እየተዳረጉ ይገኛሉ።

በመሆኑም ሁሉም ሚስዮኖች የጉዳዩ አሳሳቢነት ከግምት በማስገባት ሚስዮኑ በሚገኝበት ወይንም በሚሸፍናቸው አገራት ትምህርት የሚከታተሉ ዜጎች በጉዳዩ ላይ ዕውቀት እንዲኖራቸው አመቺ በሆኑ መንገዶች እና ሚስዮኑ በሚጠቀማቸው የማህበራዊ ሚዲያ አማራጮች በሙሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ እንዲሰራ እናሳውቃለን።

ከሰላምታ ጋር

አምባሳደር ሲራጅ ረሺድ ጀንዲ
የቆንስላ ጉዳዮች ዳይሬክተር ጀነራል

ግልባጭ ፡-

- ለዜጎች መብት ማስከበር ዳይሬክቶሬት
  የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
  <u>አዲስ አበባ</u>

Filwuha, Addis Ababa,Ethiopia. P.O.Box 393
Call: +251 115 51 73 45 | Fax: +251 115 51 43 00
Email:- Info@mfa.gov.et
Web:- www.mfa.gov.et